የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፩
አዲስ አበባ ጥቅምት ፳፮ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

25th Year No.1
ADDIS ABABA 5th Novemeber 2018

## ማውጫ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፴፩/፪ሺ፲፩ ዓ.ም

የመሬት ባንክና ልማት ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ……………ገፅ ፲ሺ፭፻፶፱

## CONTENT

Council of Ministers Regulation No.431/2018

Land Bank and Development Corporation Regulation Council of Ministers Regulation…………….......page 10559

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፴፩/፪ሺ፲፩

## የመሬት ባንክና ልማት ኮርፖሬሽንን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፱፻፲፮/፪ሺ፰ (እንደተሻሻለ) አንቀፅ ፭ እና በመንግስት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ አንቀጽ ፵፯(፩)(ሀ) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የመሬት ባንክና ልማት ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፴፩/፪ሺ፲፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### ፪ .መቋቋም

፩/ የመሬት ባንክና ልማት ኮርፖሬሽን (ከዚህ በኋላ ኮርፖሬሽን እየተባለ የሚጠራ) የፌደራል መንግስት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።

፪/ ኮርፖሬሽኑ በመንግስት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ መሰረት ይተዳደራል።

Council of Ministers Regulation No.431/2018

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO ESTABLISH LAND BANK AND DEVELOPMENT CORPORATION

This Regulation is issued by the Council of Ministers of the Federal Democratic Republic of Ethiopia pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 916/2015 and Article 47 (1) (a) of the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

### 1. Short Title

This Regulation may be cited as the "Land Bank and Development Corporation Council of Ministers Regulation No. 431/2018".

### 2. Establishment

1/ A Land Bank and Development Corporation (hereinafter the "Corporation") is hereby established as a Federal Government public enterprise.

2/ The Corporation shall be governed by the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

**፫.<u>ተቆጣጣሪ ባለስልጣን</u>**

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን የኮርፖሬሽኑ ተቆጣጣሪ ባለስልጣን ይሆናል።

**፬.<u>ዋና መስሪያ ቤት</u>**

የኮርፖሬሽኑ ዋና መስሪያ ቤት አዲስ አበባ ሆኖ እንዳስፈላጊነቱ ቅርንጫፎችን በሌሎች ከተሞችም ሊከፍት ይችላል።

**፭.<u>ዓላማ</u>**

ኮርፖሬሽኑ በፌደራል መንግሰት መስሪያ ቤቶችና የልማት ድርጅቶች ስር የሚገኙ ይዞታዎችን በተመለከተ የሚከተሉት አላማዎች ይኖሩታል፡-

፩/ ይዞታዎችን አንድ በአንድ መለየት፤

፪/ ይዞታዎችን መቁጠር እና ካርታ እንደኖራቸው ማድረግ፤

፫/ ይዞታዎችን በአግባቡ በማልማት እና በማስተዳደር መንግስት ከዘርፉ ማግኘት የሚገባውን ሁሉን አቀፍ ጥቅሞች እንዲያገኝ ማስቻል፤

፬/ ይዞታዎች ለሚሰጡት አገልግሎት ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር በሚያስችል መልኩ ማልማት፤

፭/ ይዞታዎችን አቀናጅቶ በመምራት ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጠቀሜታ እንዲሰጡ ማስቻል፤

፮/ ይዞታዎች ወደ ግል ይዞታነት ሲተላለፉ የመንግሰት ጥቅም እንዲጠበቅ ማድረግ፤

፯/ በሁሉም የፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቶችና የልማት ድርጅቶች የተያዙ ይዞታዎች መለየት ፤የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በራሱ ስም ማሰራት፤ ቀደም ብሎ የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያላቸውን ይዞታዎች ወደ ራሱ ሥም ማዞር፤ ለውሳኔ የሚረዳ በማዕከላዊነት የተደራጀ መረጃ መያዝ፤

፰/ በተለዩት የፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቶችና የልማት ድርጅቶች ይዞታዎች ባለቤት ሆኖ ከሌሎች ባለሐብቶች ጋር በጋራ ወይም በተናጥል ማልማት፤ መቆጣጠር ፤ማስተዳደር።

**3. <u>Supervising Authority</u>**

The Ethiopian Investment Commission shall be the supervising Authority of the Corporation.

**4. <u>Head Office</u>**

The Corporation shall have its head office in Addis Ababa, and may have branch offices elsewhere in other parts of the country as may be necessary.

**5. <u>Purpose</u>**

The Corporation shall have the following purposes regarding landholdings under Federal Government agencies and public enterprises:

1/ To identify each land holding;

2/ To identify and tally landholdings to ensure that they are issued with landholding certificates;

3/ To enable the government to get the maximum benefit possible from the resource by properly developing and managing landholdings;

4/ To develop the landholdings in a manner that facilitates the services Federal Government agencies and public enterprises provide;

5/ To enable the delivery of higher economic and social benefits by employing harmonized management of landholdings;

6/ To ensure the protection of government interests where landholdings are transferred to private possession.

7/ To identify all landholdings under Federal Government agencies and public enterprises and take landholding certificate in its name; to ensure the transfer of previously issued landholding certificates to its name; to have centralized data to help decision-making;

8/ To develop through joint venture with other investors or unilaterally, control and manage as holder lands identified as holdings of Federal Government agencies and public enterprises.

**፰. ካፒታል**

፩/ ኮርፖሬሽኑ የተፈቀደ ካፒታል ብር ፭ ቢሊዮን (አምስት ቢሊዮን )ሲሆን ከዚህ ዉስጥ ብር ፩ ቢሊዮን ፪፻፶ ሚሊዮን (አንድ ቢሊዮን ሁለት መቶ ሃምሳ ሚሊዮን )ብር በጥሬ ገንዘብና በአይነት ተከፍሏል።

፪/ ኮርፖሬሽኑ በጀት በራሱ ያመነጫል፤ያስተዳድራል።

**፱ .ኃላፊነት**

ኮርፖሬሽኑ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም።

**፲. ኮርፖሬሽኑ የሚቆይበት ግዜ**

ኮርፖሬሽኑ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል።

**፲፩. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ጥቅምት ፳፮ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም**

**አብይ አህመድ (ዶ/ር)**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ጠቅላይ ሚኒስትር**

**8. Capital**

1/ The authorized capital of the Corporation is Birr five billion Birr (5,000,000,000) of which Birr one billion two hundred fifty million (1,250,000,000) is paid up in cash and in kind.

2/ The Corporation shall generate its budget from own sources and administer same.

**9. Liability**

The Corporation shall not be liable beyond its total assets.

**10. Duration of the Corporation**

The Corporation is established for an indefinite period duration.

**11. Effective Date**

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 5th Day of November 2018.**

**ABIY AHMED (DR.)**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**